ARTISTIC PRINTERS 327 J



መልእክት ፡ ዳግማዊ ።

ንዑ ፡ ትርአዩ ።

ሕገ ፡ ፈቃድ ።

# የምንኵስና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ብያኔ ።

ከአባ ፡ ፊልጶስ ፡ ተጻፈ ።

www.ethiopianorthodox.org



መልእክት ፡ ዳግማዊ ።

ንዑ ፡ ትርአዩ ።

ሕገ ፡ ፈቃድ ።

# የምንኵስና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትና ፡ ብያኔ ።

ከአባ ፡ ፊልጶስ ፡ ተጻፈ ።

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ሊሚትድ ፡ ቍ ፡ 327

፲፱፻፷፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ታተመ ።

ተነትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ አመ ፡ ሠላሳ ፡ ወተስዐቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ቁጥር 2748/777/61

ሞዴል 35

አ.አ. ጥር 16 ቀን 1961 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ዋና ጽሕፈት ቤት ።

ለብፁዕ አቡነ ፊልጶስ
አዲስ አበባ:-

ብፁዕ ሆይ፣

"ሕገ ፈቃድ" በሚል አርእስት ስላዘጋጁት ጽሑፍ ጥር ወሬ ታህሣሥ 2 ቀን 1961 ዓ.ም. በጻፉልን መሠረት ጽሑፉ ሊቃውንት ጉባዔ ተሳታፊ ከተመረመረ በኋላ የተሰጠው አስተያየት ጥር 1 ቀን 61 ዓ.ም. በቁጥር 6/61 ከተጻፈ ደብዳቤ ጋር ስላቀረበልን የጉባዔው አስተያየት የሠፈረበትን 1 ገጽ ትክክል ግልባጭና የተመረመረው ዋናው ጽሑፍ ከዚሁ ጋር ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን ለብፁዕነትዎ እንገልጻለን::

ለብፁዕነትዎ ቡራኬ ይድረስን::

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911850113
0111271609
D.N Solomon Yohannes



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ በሰባዔ ፡ ውስጥ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ ክፍል ፡ የተደረገ ፡ ስብሰባ ።

የጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ አያሌው ፡ ታምሩ ፡

» አባል ፡ መምህር ፡ ጌራ ፡ ወርቅ ፡ ገብረ ፡ እግዚአ ብሔር ፡

» አባልና ፡ ጸሓፊ ፡ ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጐሹ ፡

ሆነው ፡ በተሰበሰቡበት ፡ «ሕገ ፡ ፊቃድ» ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንድንመረምር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መንግሥት ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዋና ፡ ጽ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ 2051/777/61፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ጽሑፉ ፡ ለጉባኤው ፡ ቀርቦ ፡ በንባብ ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ የሚከተለው ፡ አስተያየት ፡ ተሰጠ ።

## አስተያየት ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ከሕገ ፡ አበው ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ ትምህርትን ፡ ምክርን ፡ ማመዛዘንን ፡ ብያኔን ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ፤ በተለይም ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናን ፡ ለሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ የመጻሕፍትን ፡ አሳብ ፡ በማጠቃለል ፡ እውነተኛውን ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተ ምር ፡ ቀጥተኛውን ፡ መንገድ ፡ ዐላማ ፡ የሚያመለክት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሲሆን ፡ በሕገ ፡ ምንኵስና ፡ እጠቀማለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ለማግኘት ፡ ሲሻ ፡ ድቀት ፡ ቢያጋጥመው ፡ እደብቃለሁ ፡ በማለት ፡ በሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ ከከባድ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቅ ፡ የሚያስጠነቅቅና ፡ ሌላውም ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ በመፍረድ ፡ እንዳይፈረድበት ፡ ከፍርድ ፡ እንዲርቅ ፡ የሚመክር ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳውያን ፡ አባሎቿን ፡ በሚገባ ፡ ጠብቃ ፡ እንድትይዝ ፤ የማንኛውም ፡ አባል ፡ መብቱ ፡ ተጠብቆለት ፡ እንዲኖር ፤ እንዲሁም ፡ ከመጽሐፉ ፡ ተጽፎ ፡ ሳለ ፡ ሳይሠራበት ፡ የኖረ ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራበት ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጥ ፡ የተብራራ ፡ አሳብ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንና ፡ ገዳማውያን ፡ አባሎቿን ፡ የሚጠቅም ፤ ሀገርንና ፡ ክብሯን ፡ የሚያስጠብቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቢታተም ፡ ይጠቅማል ፤ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያሳብ ፡ መነሻነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ መነኮሳት ፡ ኑሮ ፡ የሚጠቅም ፡ ሕግ ፡ ብታወጣ ፡ አሳቡ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ለስሟ ፡ ለታሪኳና ፡ ለክብሯ ፡ ጠቃሚ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይታሰብበት ፡ ዘንድ ፡ አሳባችንን ፡ ከዐላማው ፡ ጋራ ፡ በማስተባበር ፡ አቅርበናል ፡ ሲል ፡ ጉባኤው ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጥቷል ።

ፊርማ ፡

ሰብሳቢውና ፡ አባሎቹ ፡ በሙሉ ።

መልእክት ፡ ዳግማዊ ።

ንዑ ፡ ትርአዩ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

# ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ምንኵስና ።

፩ ፤ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ባሕርያዊ ፡ ግብር ፡ ከሚያስገድደው ፡ ሥራ ፡ ተወስኖ ፡ ለመኖር ፡ በሕገ ፡ ልቡናው ፡ ተመራምሮ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የሥጋዬን ፡ ፈቃድ ፡ እየፈጸምሁ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ከምኖር ፡ ይልቅ ፡ ከዚህ ፡ ከሥጋዊ ፡ ፈቃድና ፡ ከምኞቱም ፡ ተለይቼ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየለመንሁ ፡ ልኑር ፡ ብሎ ፤ በመንፈሳዊ ፡ ኀልዮ ፡ ሥርዐተ ፡ መላእክትን ፡ ሥርዐት ፡ አድርጎ ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ሕግ ፡ መኖርን ፡ መርጦ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁንብኝ ፡ ብሎ ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋራ ፡ ተነጋግሮ ፡ አንተው ፡ አስችለኝ ፡ በማለት ፡ የሚወስነው ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ ሁሉም ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ሕግ ፡ ጠባያዊ ፡ ሕግ፡ ፈቃዳዊ ፡ አለ ።

፪ ፤ ሕግ ፡ ጠባያዊ ፡ ፈጣሪ ፡ አምላክ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርአያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ በምሳሌው ፡ አክብሮ ፡ በፈጠረው ፡ ጊዜ ፡ መሬትን ፡ ከነባሕርዩ ፡ አከናውኖ ፡ ሠራውና ፡ ተራቢ ፡ ተጻሚ ፡ ባሕርይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሆነ ፡ ማለት ፡ ምግብ ፡ የሚያሻው ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆ ፡ ለሕይወተ ፡ ሥጋው ፡ የሚያሻውን ፡ የመባልዕት ፡ መሰናዶ ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ይህን ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶታል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መብል ፡ ሕግ ፡ ጠባያዊ ፡ መሆኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያስረዳናል ፤ ከምግብ ፡ መከልከል ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መረዳት ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ እንላለን ።

፫ ፤ ስለዚህ ፡ ከፈጣሪ ፡ የታዘዘው ፡ ሁሉ ፡ ሕግ ፡ አምላካዊ ፡ ሲሆን ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ይሁንብኝ ፡ ብሎ ፡ የሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ ፈጣሪ ፡ ጌታ ፡ የሰው ፡ አባት ፡ አዳምን ፡ በፈጠረው ፡ ጊዜ ፡ የመዋለድ ፡ ማለት ፡ የሩካቤ ፡ ፈቃድ ፡ (የጋብቻ) ፡ የፍትወትን ፡ ባሕርይ ፡ በአካሉ ፡ ውስጥ ፡ አስማምቶ ፡ የፍትወት ፡ ባሕርያዊ ፡ ዘር ፡ ያለው ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ፈጠረው ፡ ዐውቆ ፡ አዳም ፡ ብቻውን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ደግ ፡ አይደለምና ፡ የቅርብ ፡ ረዳት ፡ የምትሆን ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ ሚስት ፡ እንፍጠርለት ፡ ብሎ ፡ ባሕርያዊ ፡ ፈቃዱን ፡ የሚፈጽምባት ፡ ሚስት ፡ ሔዋንን ፡ ከሥጋው ፡ ከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ነግሮናል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አውስቦ ፡ (ጋብቻ) ፡ ሕግ ፡ ጠባይዓዊ ፡ (ባሕርያዊ) ፡ መሆኑን ፡ ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ሲያስረዳን ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ የመኖር ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ወዶ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። ባሕርያዊ ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ በውዴታው ፡ የሚሠራው ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ።



፬ ፤ ስለዚህ ፡ ነው ፡ የመጽሐፉን ፡ መግቢያ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ (የጋብቻን ፡ ሥርዐት) ፡ መሠረተ ፡ ሕግ ፡ ያልነው ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ በምንኵስና ፡ ሥርዐት ፡ መኖር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በውዴታው ፡ የሚከተለው ፡ ከፈጣሪ ፡ ግዴታ ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አበው ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ብለውታል ።

፭ ፤ ይህም ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ በመንኖ ፡ ጥሪት ፡ ተወስኖ ፡ የመኖር ፡ ሥርዐትም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሊሆንብን ፡ አይችልም ፤ የኋላ ፡ ሰዎች ፡ የፈጠሩት ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ጥንትም ፡ ከቀደሙት ፡ አበው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ተለይተው ፡ ከሴት ፡ ርቀው ፡ ንጽሕናን ፡ ጠብቀው ፡ ከዓለማዊ ፡ ፍትወት ፡ (ምኞት) ፡ ተገልለው ፡ በየዋሻው ፡ እየተሰወሩ ፡ በብቸኝነት ፡ ይኖሩ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ለዚህም ፡ መረጃ ፡ የመልከጼዴቅን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ኑሮ ፡ ብንመለከት ፡ ያስረዳናል ፡ (ዘፍ፲፬ ፡ ፲፰ ። ዕብ፯ ፡ ፩ ፡ ፲) ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

# መንኖ ፡ ጥሪት ።

፩ ፤ ይህም ፡ የመንኖ ፡ ጥሪት ፡ ሥርዐት ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ሆኗል ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ትምህርቱን ፡ ሲገልጥ ፤ «ብፁዓን ፡ ነዳያን ፡ በመንፈስ ፡ ከሀብትና ፡ ከንብረት ፡ ተለይተው ፡ የፈቃድ ፡ ነዳያን ፡ የሆኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ አለ» ፡ (ማቴ፭ ፡ ፫) ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ ፤ ቀጥሎም ፡ አንድ ፡ የሥጋዊ ፡ ሹመት ፡ ፈቃድ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ጌታችን ፡ ምድራዊ ፡ ንጉሥ ፡ መስሎት ፡ ወደምትሄድበት ፡ ሁሉ ፡ እከተልኻለሁ ፡ ቢለው ፡ «ለቀበሮች ፡ ጉድጓድ ፡ አላቸው ፤ ለሰማይ ፡ ወፎችም ፡ መስፈሪያ ፡ ጐጆ ፡ አላቸው ፤ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ ስንኳ ፡ የለውም» ፡ ብሎ ፡ የዓለምን ፡ ከንቱነት ፡ አስተምሯል ።

፲ ፤ ቀጥሎም ፡ ሐዋርያትን ፡ መረጠና ፡ ለተከተሉት ፡ ሁሉ ፡ ምድራዊን ፡ ሀብትና ፡ ጌትነት ፡ ተስፋ ፡ እንዳያደርጉ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ አስተምሯቸዋል ፤ «በኋላዬ ፡ ሊመጣ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ይካድ ፤ መስቀሉንም ፡ (መከራን) ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡ ያጠፉታል ፤ ስለኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ነፍሱን ፡ የሚያጠፉ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ያድናታል ። ሰው ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ቢያተርፍ ፡ ነፍሱንም ፡ ቢያጐድል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፤ ሰውስ ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ ይሰጣል ፡ (ማር፰ ፡ ፴፬-፴፯) ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ከመላእክቱ ፡ ጋራ ፡ ባባቱ ፡ ክብር ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ለሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ያስረክበዋል» ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ተለይቶ ፡ ሥጋዊ ፡ መሻቱን ፡ (ምኞቱን) ፡ ለመንፈሳዊው ፡ ዓለም ፡ ምኞት ፡ ለውጦ ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ ባይተዋር ፡ (ባዕድ) ፡ ሆኖ ፡ ከሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ተለይቶ ፡ መኖርን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካለው ፡ ፍትወትና ፡ ምኞት ፡ ከሥጋዊ ፡ ዕድል ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ለዘላለም ፡ የማያልፍ ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ እንደሚያስገኝ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አስተምሮ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ክብርና ፡ ብዕል ፡ ሚዛን ፡ ቢመዘን ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የሌ



ለው ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ «ምንት ፡ ይበቍዖ ፡ ለሰብእ ፡ ለእመ ፡ ኰሎ ፡ ዓለመ ፡ ረብሐ ፡ ወነፍሶ ፡ ሀጕለ» ፡ በማለቱ ፡ በዓለም ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ ለነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ለውጥ ፡ እንደማይበቃ ፡ ያስረዳናል ።

፲፩ ፤ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የቃሉን ፡ ትምህርት ፡ ሰምተው ፡ ከተከተሉት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ «እንሆ ፡ እኛ ፡ ሁሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንኽ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ሲያስረዳው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ «እውነት ፡ እላችኋለሁ ፤ ማንም ፡ ስለኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌልም ፡ ቤቱን ፡ ወንድሞቹን ፡ እኅቶቹን ፡ አባት ፡ እናቱንም ፡ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ፡ እርሻንም ፡ የሚተው ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከስደት ፡ ጋራ ፡ ቤቶችን ፡ ወንድሞችን ፡ እኅቶችን ፡ እናቶችንም ፡ ልጆችንም ፡ እርሻንም ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ የማይቀበል ፡ ማንም ፡ የለም» ፡ በማለቱ ፡ (ማር፲ ፡ ፳፱-፴) ።

፲፪ ፤ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲኖር ፡ በሥጋዊ ፡ ኑሮው ፡ ከሚያገኘው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ተለይቶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሥጋ ፡ ከማገኘው ፡ ክብርና ፡ ብዕል ፡ ሁሉ ፤ ክርስቶስን ፡ በመከተል ፡ በሰማያዊ ፡ ዓለም ፡ የማገኘው ፡ ጸጋና ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ክብር ፡ ይበልጥብኛል ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዝርዝር ፡ የተነገረውን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያገለገለ ፡ ቢኖር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ይበልጠውን ፡ ብዙ ፡ ወዳጅና ፡ ዘመድም ፡ እንደሚያገኝ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልፋል ፡ ይጠፋል ፡ የማይባል ፡ ዘላለማዊ ፡ የነፍስን ፡ ሕይወት ፡ እንደሚቀበል ፡ ያስረዳናል ።

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፡ ስለዚህ ፡ ሐዋርያት ፡ ከጌታችን ፡ የተነገረውን ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዐላማ ፡ አድርገው ፡ በኋላዬ ፡ ሊመጣ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ (መከራውን) ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ዓለሙን ፡ ከነጣዕሙ ፡ ንቀው ፡ ራሳቸውን ፡ ለክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ሕይወታቸውን ፡ ሰጥተው ፡ አልፈውታል ።

፰ ፤ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ የሐዋርያትን ፡ ትምህርት ፡ ተቀብለው ፡ በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ምእመናን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራን ፡ ታግሠው ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ተወስነው ፡ ለወንጌል ፡ መልእክት ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ የተወደዳችሁ ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ፤ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ ተወስኖ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ሆኖ ፡ የመኖር ፡ ሥርዐት ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ ልማድ ፡ መሆኑ ፡ በነመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሥርዐት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

፪ ፤ በሐዲስ ፡ ኪዳንም ፡ ድንግልና ፡ ከላይ ፡ በተነገረው ፡ በጌታችን ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ከሐዋርያት ፡ ገሮምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ መነኮሳት ፡ የደረሰ ፡ የንጽሕና ፡ የቅድስና ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ አበው ፡ ከዓለማዊ ፡ ፍቅር ፡ ርቀው ፡ የሰማያዊውን ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ እጅግ ፡ ተጠቅመውበታል ።



፫ ፤ ይኸውም ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አስገዳጅ ፡ አይደለም ፤ ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ የሚባልበትም ፡ ምክንያት ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባልና ፡ ሚስትን ፡ አንድነት ፡ ባስተማረበት ፡ አንቀጽ ። «ፈጣሪ ፡ በመገርመሪያ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አደረጋቸው ፤ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፤ ከሚስቱም ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፤ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ አላነበባችሁምን ፤ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሁለት ፡ አይደሉም ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረገውን ፡ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ አይለየው ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፤ ያለዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሚስቱን ፡ ፈቶ ፡ ሌላይቱን ፡ የሚያገባ ፡ ሁሉ ፡ ያመነዝራል ፤ የተፈታችውንም ፡ የሚያገባ ፡ ያመነዝራል ፡ እያለ ፡ የባልና ፡ ሚስትን ፡ ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ ያለመለያየትን ፡ ሕግ ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ሥርዐት ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ መጋባት ፡ ደግ ፡ አይደለም ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ (አለማግባት) ፡ ለተሰጣቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሁሉ ፡ የሚቻል ፡ አይደለም ፡ አለና ፡ ምክንያቱንም ፡ ሲያስረዳ ፡ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ራሳቸውን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ ፡ አሉ ፤ ሊቀበለው ፡ (ሊታገሠው) ፡ የሚችል ፡ ይቀበለው ፡ (ይታገሠው) ፡ በማለቱ ፡ ድንግልና ፡ የፈቃድ ፡ እንጂ ፡ ግዴታ ፡ አለመሆኑን ፡ አስተምሯል ፡ (ማቴ ፲፱ ፡ ፬-፲፪) ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ የሥጋን ፡ ባሕርይ ፡ ፈቃድ ፡ መታገሥ ፡ ጽኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገልጾ ፡ ፈተናውን ፡ እችላለሁ ፡ ያለ ፡ ግን ፡ ይቻል ፡ በማለቱ ፡ ፈቃዱን ፡ ለመራጩ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፤ እንደዚሁ ፡ ለምእመናን ፡ ሲያስረዳ ፡ ስለ ፡ ጻፋችሁት ፡ ነገር ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ አለመ ገናኘት ፡ ለሰው ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ (ዝሙት ፡ ጠንቅ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለራሱ ፡ ሚስት ፡ ትኑረው፤ ለያንዳንዷ ፡ ደግሞ ፡ ለራሷ ፡ ባል ፡ ይኑራት ፡ አለና ፡ ምክ ንያቱን ፡ በመቀጠል ፡ ላላገቡና ፡ ለመበለቶች ፡ ግን ፡ እላ ለሁ ፡ እንደኔ ፡ ቢኖሩ ፡ ለእነርሱ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በምኞት ፡ (በፍትወት) ፡ ከመቃጠል ፡ መጋባት ፡ ይሻላልና ፡ ራሳቸውን ፡ ለመግዛት ፡ ባይችሉ ፡ ያግቡ ፡ አለና ፡ ቀጥሎ ፡ ስለ ፡ ድናግልም ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ የለ ኝም ፡ (አይደለም) ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከጌታ ፡ ምሕረትን ፡ የተ ቀበልሁ ፡ እንደ ፡ መሆኔ ፡ ምክር ፡ እመክራለሁ ።

እንግዲህ ፡ ስለ ፡ አሁኑ ፡ ችግር ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ቢኖር ፡ መልካም ፡ ነው ፤ በሚስት ፡ ታስረኽ ፡ እንደሆን ፡ ሚስትን ፡ አትሻ ፤ በሚስት ፡ አልታሰርኽ ፡ እንደ ፡ ሆንኽ ፡ ግን ፡ ብታገባ ፡ ኀጢአት ፡ አትሠራም ፤ ድንግሊቱም ፡ ብታገባ ፡ ኀጢአት ፡ አትሠራም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ያላሳብ ፡ ልትኖሩ ፡ እወዳለሁ ፤ ያላገ ባው ፡ ጌታን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኘው ፡ ያስባል ፤ ያገባው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኛት ፡ የዓለምን ፡ ነገር ፡ ያስባል ። ልቡም ፡ ተከፍሏል ፤ ያላገባች ፡ ሴትና ፡ ድንግልም ፡ በሥጋም ፡ በነፍስም ፡ እንዲቀደሱ ፡ የጌታን ፡ ነገር ፡ ያስባሉ ፤ የተጋባች ፡ ግን ፡ ባሏን ፡ እን ዴት ፡ ደስ ፡ እንደምታሰኘው ፡ የዓለምን ፡ ነገር ፡ ታስባ ለች ፤ ይህንም ፡ ለራሳችሁ ፡ ጥቅም ፡ እላለሁ ፤ በአግባብ ፡ እንድትኖሩ ፡ ሳትባክኑም ፡ በጌታ ፡ እንድትጸኑ ፡ ነው ፡



እንጂ ፡ ላጠምዳችሁ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፩ ። ፯ ፡ ፩-፲፯) ፡ እያለ ፡ መዝሙሪያ ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ ለሚስት ፡ ለልጅ ፡ ሳያስብ ፡ ከዚህ ፡ ከዓለማዊ ፡ አሳብ ፡ ነጻ ፡ ሆኖ ፡ ራሱን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ እንደሚቻለው ፤ ያገባ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ወንድም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ሐሳቡ ፡ ትዳሩን ፡ ለማሸነፍ ፡ የሚገደድ ፡ መሆኑን ፡ ያሳ ያል ።

፭ ፤ ዋናው ፡ የምክሩ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ግን ፤ ላላገቡ ፡ ግን ፡ እላለሁ ፡ እንደኔ ፡ ቢኖሩ ፡ ለነርሱ ፡ መልካም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በምኞት ፡ ከመቃጠል ፡ ማግባት ፡ ይሻላልና ፡ ራሳቸውን ፡ ለመግዛት ፡ ባይችሉ ፡ ያግቡ ፡ እያለ ፡ የራሱን ፡ ምክር ፡ ይመክራል ። ይህንንም ፡ የሰጠውን ፡ ምክር ፡ ለጐ ልማሶች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አለመሆኑንም ፡ በማስረዳት ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ በድንግልና ፡ ኑረው ፡ በሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ የተሸነፉ ፡ ሰዎች ፡ በሽምግልና ፡ ጊዜያቸው ፡ ማግባት ፡ የሚያሳፍር ፡ የሚመስላቸውን ፡ ሲመክርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ ማግባት ፡ አስቦ ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ ድንግ ልናው ፡ የሚያፍር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እንዲህ ፡ ሊሆን ፡ ይገ ባል ፤ የወደደውን ፡ ያድርግ ፤ ቢያገባም ፡ ኀጢአት ፡ የለ በትም ፤ ልቡናው ፡ ሳይናወጥ ፡ የጸና ፤ መታወክ ፡ የሌለበ ትን ፡ ግድ ፡ አይበሉት ፤ የወደደውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

ድንግልናውን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ቢወድ ፡ መልካም ፡ አደረገ ፤ በድንግልና ፡ ኑሮ ፡ ያገባም ፡ መል ካም ፡ አደረገ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይልቁንም ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ አደረገ ፡ በማ ለቱ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ውሳጣዊ ፡ ባሕርዩን ፡ መርምሮ ፡ ለኅሊናው ፡ የሚስማማውን ፡ ራሱ ፡ እንዲመ ርጥ ፡ የመንፈስ ፡ ችሎታውን ፡ መብት ፡ ይወስን ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ምክሩን ፡ ያበረክታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ አንባቢ ፡ ወንድም ፡ ሆይ ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ሕግ ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ፡ ነው ፤ ጥንቱንም ፡ ሰው ፡ ሲፈጠር ፡ ከፈጣሪ ፡ የተሰጠ ፡ ፈራጅ ፡ ኅሊና ፡ ያለው ፡ ለባዊ ፡ ፍጡር ፡ ነው ። ግላዊም ፡ ሆነ ፡ አፍአዊ ፡ ግዳጁን ፡ ለባሕርዩ ፡ የሚ ያሻውን ፡ ዐውቆ ፡ ራሱ ፡ የመምረጥ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ይመክራሉ ፡ እንጂ ፡ አያስገድዱም ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳለው ፡ ዓለማዊን ፡ ፈቃድ ፡ ትቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለገለ ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተጋድሎውን ፡ ዋጋ ፡ እንደሚያገኝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ እንደዚሁም ፡ የሰውነቱን ፡ ደካምነት ፡ አይቶ ፡ በተሰጠው ፡ ዕድል ፡ በጋብቻው ፡ ሥርዐት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ቢኖር ፡ ከጌታ ፡ የሚሰ ጠው ፡ (የሃይማኖቱ) ፡ የእምነቱ ፡ ዋጋ ፡ አይጐድልበትም ።

፪ ፤ ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ምክር ፡ እንደሚያስረዳው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ለሰው ፡ በዓለማዊነትም ፡ ሆነ ፡ በፍጹምነት ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ ያለ ውን ፡ የመንፈሱን ፡ ምርጫ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ኅሊና ፡ ዕድሉን ፡ ለመወሰን ፡ መብት ፡ አለው ፡ ብንል ፡ ስሕተት ፡ አይመስለንም ።



፫ ፤ ለሰው ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ መሠረት ፡ ጋብቻ ፡ በሁሉ ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ ለመኝታቸውም ፡ ርኵ ሰት ፡ የለበትም ፡ በተባለው ፡ ቃል ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተስ ማምተው ፡ በሚፈጽሙት ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሕጋዊ ፡ ንብረት ፡ ለማቋቋም ፡ መብት ፡ አለው ፤ ጋብቻ ፡ መሠረተ ፡ ሕግና ፡ ንጹሕም ፡ ነው ፡ እንላለን ።

፬ ፤ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ከዓለማዊ ፡ ኑሮ ፡ ይልቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮን ፡ መርጦ ፡ በድንግልና ፡ በንጽ ሕና ፡ ተወስኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያገለገለ ፡ የመኖርን ፡ ዕድል ፡ ቢመርጥም ፡ የገድሉን ፡ ዋጋ ፡ የበለጠውን ፡ ጸጋ ፡ ያገኛል ፡ እንላለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

# ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ።

፩ ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕናን ፡ ጠብቆ ፡ የመኖር ፡ ሕግ ፡ ጌታችን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሰው ፡ ሥጋ ፡ ተገልጾ ፡ ወንጌልን ፡ ባስተማረበት ፡ ጊዜ ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ የተመሠረተ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ። ጌታችን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ካረገ ፡ በኋላም ፡ ሐዋርያት ፡ ጌታ ችን ፡ ሊከተለኝ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ፡ ብሎ ፡ ባስተማራቸው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የዓለሙን ፡ ኑሮ ፡ መን ነው ፡ ከማናቸውም ፡ ከዓለማዊ ፡ ምኞት ፡ ተለይተው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ያላቸውን ፡ ጥሪት ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ አድርገው ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ድርጅት ፡ የክርስቶስን ፡ ሃይማኖት ፡ እየሰበኩ ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ሆነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያገለገሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ እንዳለፉ ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ይነግረናል ።

፪ ፤ ከሐዋርያት ፡ ቀጥለው ፡ የተነሡ ፡ አበውም ፡ ቀሲሳን ፡ እየተባሉ ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ቈራጥነት ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ክርስቶስን ፡ እየሰበኩ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ክብራቸውንና ፡ አለኝታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ ለውጠው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ የተጠቀሙ ፡ አበው ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዜና ፡ አበው ፡ ይነግረናል ።

፫ ፤ ቀጥሎም ፡ የክርስቲያን ፡ ማኅበር ፡ በበዛ ፡ ቍጥር ፡ ሥርዐት ፡ እየተሻሻለ ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አስተዳደር ፡ ደርሶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኤጲስቆጶሳት ፡ ጉባኤ ፡ እየተመራች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እድገት ፡ እየተስፋፋ ፡ በሄደ ፡ መጠን ፡ ለክርስቶስ ፡ ያደሩ ፡ ምእመናን ፡ እየበዙ ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ በአማንያን ፡ ልብ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ብርሃኑን ፡ እያበራ ፡ በመሄዱ ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ መነኮሳት ፡ ደርሶ ፡ የመነኮሳት ፡ ሥርዐት ፡ ቀጠለ ፤ ለዚሁም ፡ መነሻው ፡ ጌታችን ፡ «እመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወንዐ ፡ ትልወኒ ፤ ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ከፈቀድኽ ፡ ያለኽን ፡ ሁሉ ፡ ሸጠኽ ፡ ለድኾች ፡ ስጥ ፡ በሰማይ ፡ መዝገብ ፡ ታገኛለኽ ፤ መጥተኽም ፡ ተከተለኝ» ፡ ባለው ፡ ትምህርት ፡ መሪነት ፡ ነው ፡ (ማቴ፲፱ ፡ ፳፩) ። ስለዚህ ፡ የምንኵስና ፡ ገድል ፡ መሥራች ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ያለ ፡ ጥሪታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለነዳ



ያን ፡ ሰጥተው ፡ ዓለሙን ፡ ሸሽተው ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ በረሓ ፡ ገብተው ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስናን ፡ አቀኑ ።

፬ ፤ ምንኵስናም ፡ ማለት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚገኘው ፡ ምኞት ፡ ከሥጋዊ ፡ ብዕልና ፡ ክብር ፡ ተለይቶ ፡ ፈጣሪ ፡ ጌታን ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ እያሰቡ ፡ ከዘመድ ፡ ከወዳጅ ፡ ርቆ ፡ በርእይና ፡ በሰሚዕ ፡ ከሚነሣው ፡ ፍትወት ፡ በመሸሽ ፡ የሴት ፡ መልክ ፡ ከማይታይበት ፡ ድምፅዋም ፡ ከማይሰማበት ፡ በረሓ ፡ ወድቀው ፡ በበአት ፡ ተከተው ፡ ከዓለም ፡ ተገልለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በቁመት ፡ በስግደት ፡ እየለመኑ ፡ በተባሕትዎ ፡ (በብቸኝነት) ፡ የመኖር ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፭ ፤ ይህንም ፡ የምንኵስና ፡ ሥርዐት ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ መሥራቹ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ናቸው ። «ወዘንቱሰ ፡ ቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ አባሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መነኮሳት ፡ ኮነ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ ቅማን ፡ እምብሔረ ፡ ግብጽ ፡ እምሰሚኒ ፡ ምስር» ፡ ይላቸዋል ።

በምስር ፡ ሰሜን ፡ በምትገኘው ፡ የሀገረ ፡ ቅማን ፡ ተወላጅ ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ መሆናቸውን ፡ ገድላቸው ፡ ይነግረናል ፡ (ስንክሳር ፡ ጥር ፡ ፳፪) ። እኚህ ፡ ደገኛው ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በወንጌል ፡ «ፍጹም ፡ ልትሆን ፡ ከወደድኽ ፡ ሂድና ፡ ያለ ፡ ንብረትኽን ፡ ሸጠኽ ፡ ለነዳያን ፡ ሰጥተኽ ፡ ለራስኽ ፡ በሰማይ ፡ መዝገብ ፡ አድርግና ፡ ና ፡ ተከተለኝ» ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አስበው ፡ ካባታቸው ፡ የወረሱትን ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ሸጠው ፡ ለነዳያን ፡ መጽውተው ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ በፍጹምነት ፡ ሥራ ፡ በተባሕትዎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሲኖሩ ፡ የሰይጣናት ፡ ፈተና ፡ በተቃወማቸው ፡ ጊዜ ፡ የታ ዘዘ ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ ወጥተኽ ፡ ተመልከት ፡ እንዳላ ቸውና ፡ ከበኣታቸው ፡ ወጥተው ፡ ቢመለከቱም ፡ መል አኩ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ለብሶ ፡ ቅናት ፡ የሐንስና ፡ በመስቀልኛ ፡ የተታታ ፡ አስኬማ ፡ አድርጎ ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡ አምሳል ፡ ቆብ ፡ ደፍቶ ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ ሰሌን ፡ ሲታታ ፡ ሥራውን ፡ አሳርፎም ፡ ተነሥቶ ፡ ሲጸልይ ፡ ጸሎቱንም ፡ ሲጨርስ ፡ ተመልሶ ፡ ሰሌኑን ፡ ሲሠራ ፡ ታያቸውና ፡ እንጦንዮስ ፡ እንደዚህ ፡ አድርግ ፡ የሰይጣናትም ፡ ጦር ፡ ይጠፋልኻል ፡ አላቸው ፡ ይላል ።

፯ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ይህን ፡ ልብሰ ፡ ምንኵስና ፡ እርሳቸው ፡ ከመልአክ ፡ አግኝተው ፡ ለበሱና ፡ ረድ አቸው ፡ ለነበረው ፡ ለአባ ፡ መቃርስም ፡ አልባሰ ፡ ምንኵ ስናን ፡ አለበሱት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ትሩፋታቸውና ፡ ገድ ላቸው ፡ በክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲ ያን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ቅንአት ፡ እየተነሣ ፡ የአባ ፡ እንጦንዮስን ፡ ዐላማ ፡ ተከትሎ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ሙላት ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ የሚጐርፍ ፡ ሆነ ፡ እነዚህም ፡ መንፈሳውያን ፡ አበው ፡ መነኮሳት ፡ ሥርዐተ ፡ ገዳም ፡ ሠርተው ፡ ማኅበራዊ ፡ አንድነታቸውን ፡ አጽንተው ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ምድ ራውያን ፡ መላእክት ፡ የሚያሰኝ ፡ ዝና ፡ አትርፈዋል ፡ ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ ዜና ፡ አበውን ፡ መመልከት ፡ ያሻል።

፰ ፡ ይህም ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ በኢትዮጵያችንም ፡ በቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ (አባ ፡ ሰላማ) ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ተሰበከ ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ የመጡ ፡



ተስዐቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስናን ፡ እንዳቀኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አበው ፡ መናንያን ፡ መነኮሳት ፡ ሕጉን ፡ ተቀብለው ፡ በዚሁ ፡ በፍጹምነት ፡ በሥርዐተ ፡ ምንኵስና ፡ ዐላማ ፡ ተመርተው ፡ ከኀላፊው ፡ ዓለም ፡ ፈቃድ ፡ ተለይተው ፡ ገዳማትን ፡ ካቀ ኑበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስካሁንም ፡ የእንጦንስንና ፡ የመ ቃርስን ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሥርዐተ ፡ ማኅበርን ፡ ጠብቀው ፡ የሚኖሩበት ፡ ምንኵስ ናን ፡ አጽንተው ፡ በማኅበራዊው ፡ ሕግ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ብዙ ፡ ገዳማት ፡ አሉን ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ይኸውም ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በትምህርቱ ፡ «እመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሑር ፡ ሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነ ዳያን ፡ ወነዐ ፡ ትልወኒ ፡ ፍጹም ፡ ልትሆን ፡ ከወደድኽ ፡ ሂድና ፡ ያለ ፡ ንብረትኽን ፡ ሸጠኽ ፡ ለነዳያን ፡ ስጥና ፡ መጥተኽ ፡ ተከተለኝ» ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አባ ፡ እንጦንስ ፡ ያቀኑት ፡ ከዓለማዊ ፡ ፈቃድ ፡ ተለይተው ፡ ንጽ ሕናን ፡ ጠብቀው ፡ በዐይን ፡ ከሚታየው ፡ በጆሮ ፡ ከሚሰ ማው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ርቀው ፡ በርእይና ፡ በሰሚዕ ፡ ከሚ መጣው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍትወት ፡ ተለይተው ፡ የሚኖሩ ፡ ፈቃደኞች ፡ የሚፈጽሙት ፡ የፍጹማን ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፪ ፡ አበው ፡ ሠለስቱ ፡ ምእትም ፡ «ምንኵስናሰ ፡ ዘእምፈቃድ ፡ ይእቲ ፡ ወአኮ ፡ በግብር ፡ ምንኵስና ፡ የፈቃድ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ በግዴታ ፡ የምትሆን ፡ አይደለ

www.ethiopianorthodox.org

ችም» ፡ ብለዋታል ። ቀጥሎም ፡ «ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ አሐዱ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ይመንኵስ ፡ ወይንበር ፡ ውስቴቱ ፡ ይሕትቶ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ ሐተታ ፡ ጽኑዐ ፡ እምአይቴ ፡ ውእቱ ፤ ወምንት ፡ ግብሩ ፡ ወበምንት ፡ ተማሕፀነ ፡ ኀበ ፡ ምኔት» ፡ እንዳለ ። አንድ ፡ ሰው ፡ መንኵሶ ፡ በገዳም ፡ ለመኖር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የደብሩ ፡ አለቃ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሥራውም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ በገዳም ፡ መኖርን ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ይጠይቀው ፤ (ይመርምረው) ፡ ብለዋል ፡ (ፍ ፡ ነ ፡ አንቀጽ ፡ ፲) ።

፫ ፤ አበው ፡ ገዳማውያንም ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ማናቸውም፡ ልመንኵስ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ገዳም፡ በመጣ፡ ጊዜ ፡ የመጣበትን ፡ ምክንያት ፤ ጠባዩንና ፡ ግብሩን ፡ ችሎታውንም ፡ ሳይመረምሩ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ዕለቱን ፡ አይመነኵስም ። ካንድ ፡ ዓመት ፡ ያላነሰ ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ በገዳም ፡ ተቀምጦ ፡ ገዳሙን ፡ እያገለገለ ፡ ግብረ ፡ ገብነቱ ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ በረድእነት ፡ አመክሮ ፡ አድርገውለት ፡ ለምንኵስና ፡ የተገባ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያለው፡ሰው፡ሆኖ፡የተገኘ፡እንደ፡ሆነ፡ማኅበሩ፡ሁሉም፡ ይገባዋል ፡ ብለው ፡ ሲመሰክሩለት ፡ ነው ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስናን ፡ ፈጽመው ፡ ቆብ ፡ የሚያለብሱት ።

፬ ፤ በመጽሐፈ ፡ ምንኵስናም ፡ «ወይንበር ፡ ዓመተ ፡ ፍጽምተ ፡ በማእከለ ፡ አኀው ፡ እስከ ፡ ይትአምር ፡ ሠናዩ ፡ ወእከዩ ፤ ወእምዝ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ይመንኵስ» ፡ ይላል ። ስለዚህ ፡ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ፡ ትቶ ፡ ከችግር ፡ ሸሽቶ ፡ የመጣ ፡ (ዘጐየ ፡ እምዐጸባ) ፡ እንዳይሆን ፡ ከብዙ ፡ ምርመራና ፡ ጥንቃቄ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የሚመነኵሰው ፡



እንጂ ፤ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ እንደሚታየው ፡ ለድንገተኛ ፡ ተሳላሚና ፡ ለአድሮ ፡ ሀያጅ ፡ ሰው ፡ ምንኵስና ፡ አይፈቀድም ።

፭ ፤ የአመክሮውን ፡ ፈተና ፡ ፈጽሞ ፡ እንዲመነኵስ ፡ በተፈቀደለት ፡ ጊዜም ፡ የሚከተለው ፡ ጥያቄ ፡ ይነገረዋል።

«ዓለሙንና ፡ በዓለሙ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ፍትወት ፡ ሁሉ ፡ ትቻለሁ» ።

«ንጽሕናን ፡ ትሕትናን ፡ መቲረ ፡ ፈቃድን ፡ (መታዘዝን) ፡ እጠብቃለሁ» ።

«ከገዳሙ ፡ ከማገኘው ፡ መቍነን ፡ በቀር ፡ ከማኅበሩ ፡ የተለየ ፡ ጥሪት ፡ አላበጅም» ።

«መንኖ ፡ ጥሪትን ፡ እጠብቃለሁ» ።

እንደ ፡ ማኅበሩ ፡ ሕግ ፡ የቆመውን ፡ ቍረጥ ፤ የተጋደመውን ፡ ፍለጥ ፡ ቢሉኝ ፡ በትሕትና ፡ ታዝዤ ፡ እፈጽማለሁ ፤ ነፍሴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥጋዬን ፡ ለማኅበር ፡ ሰጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ በማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ይመነኵሳል ።

፮ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውን ፡ ቃል ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ፡ የተቀበለ ፡ መነኵሴ ፡ ለምንኵስና ፡ ገድል ፡ ዋና ፡ መሠረቱ ፡ ተአገዞና ፡ አጽንዖ ፡ በኣት ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ለሞፍቅደ ፡ ደብር ፡ ማለት ፡ ለገዳሙ ፡ ጉዳይ ፡ ከሊቀ ፡ ማኅበሩ ፡ የታዘዘ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የገዳም ፡ መነኵሴ ፡ ሆኖ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ከገዳም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሊወጣ ፡ አያሰናብቱም ።

አበው ፡ መነኮሳት ፡ አጽንዖ ፡ በኣትን ፡ ያጸና ፡ መነኵሴን ፡ ሌላው ፡ ፈተና ፡ ድል ፡ ሊነሣው ፡ አይችልም ፡ ይላሉ ፤ መነኵሴ ፡ ከበኣቱ ፡ ካልወጣ ፡ በቀር ፡ ከርእይና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከሰሚዕ ፡ የሚነሣ ፡ የፈቲው ፡ ፈቃድ ፡ አያገኘውም ፤ ከሰውነት ፡ ባሕርዩ ፡ የሚነሣሣ ፡ የኀልዮ ፡ ኀጢአት ፡ መኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆንም ፡ በማየትና ፡ በመስማት ፡ ከሚነሣው ፡ ፈተና ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ አይሆንም ።

ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ፈተና ፡ ለመዳን ፡ ነው ፡ ደገኞቹ ፡ አበው ፡ አጽንዖ ፡ በአትን ፡ አጥብቀው ፡ የሚያዙት ።

፯ ፤ አበው ፡ መነኮሳትም ፡ ምሳሌ ፡ ሲሰጡ ፡ አንበሳ ፡ ከዱሩ ፡ ዓሣ ፡ ከባሕሩ ፡ ካልወጡ ፡ አይሞቱም ፤ መነኰሲም ፡ ከደብሩ ፡ ካልወጣ ፡ የኀጢአት ፡ ድቀት ፡ አያገኘውም ፤ በኀጢአት ፡ አይወድቅም ፡ ይላሉ ።

ስለዚህ ፡ መነኮሳት ፡ እንደ ፡ አበው ፡ ሕግ ፡ በገዳማቸው ፡ ተወስነው ፡ ካልተቀመጡ ፡ በቀር ፡ ገዳሙን ፡ ለቀው ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ከኖሩ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩትን ፡ ጠብቀው ፡ ይኖራሉ ፤ ማለት ፡ ዓሣ ፡ ከባሕር ፡ ወጥቶ ፡ ይኖራል ፤ አይሞትም ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ይቈጠራል ፡ ይላሉ ። ይህንም ፡ ስንል ፡ ለገዳማቱ ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ የመሰለ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ተልእኮ ፡ በዓለማውያን ፡ መካከል ፡ ለሚፈጸም ፡ ተግባር ፡ በከተማ ፡ በመንግሥት ፡ አደባባይ ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ የሚገኙበት ፡ ምክንያት ፡ መኖሩ ፡ ቢታወቅም ፤ እንደ ፡ አበው ፡ ትእዛዝ ፡ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ ብቻውን ፡ እንዲላክ ፡ አይፈቀድም ፤ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ እየሆኑ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተጠባበቁ ፡ ቀን ፡ ተግባራቸውን ፡ አብረው ፡ ሲከታተሉ ፡ እየዋሉ ፡ ማታ ፡ የሚገቡበት ፡ ስፍራ ፡ ለመንፈሳውያን ፡ በተወሰነ ፡ እንደ ፡ ገዳም ፡ ሕግ ፡ በተከበረ ፡ ከዓለማውያን ፡ ሰፈር ፡ በተለየ ፡ በገለልተኛ ፡ ማደሪያ ፡ ቦታ ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።



## ምዕራፍ ፡ ፺ ።

፩ ፤ ይኸውም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ለዝርዝር ፡ ተላላኪ ፡ ላንዳንድ ፡ መነኮሳት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጠቅላላው ፡ ዓለመ ፡ መነኮሳትን ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ ነው ።

በገዳማት ፡ ተወስነው ፡ ከሚኖሩ ፡ ከማኅበረ ፡ መነኮሳት ፡ ይዞ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ እስከሚያስተዳድሩ ፤ እስከ ፡ አበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አስተዳደር ፡ ድረስ ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ ነው ። ቅድስናቸው ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ በትረ ፡ ያሬኮችና ፡ መሰሎቻቸው ም ፡ በዓለም ፡ መካከል ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማ ፤ መኖሪያቸው ፡ ሥርዐተ ፡ ገዳምን ፡ የጠበቀ ፡ ከወንድ ፡ አገልጋይ ፡ በስተቀር ፡ የሴት ፡ አገልጋይ ፡ የማትደርስበት ፡ በቅድስና ፡ የተከለለ ፤ እጅግም ፡ የታፈረ ፡ ገዳም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የአበው ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፪ ፤ ይህም ፡ የመንፈሳውያን ፡ አበው ፡ አስተዳደር ፡ ሕግ ፡ መሠረቱ ፡ ከገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዛሬም ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ የሌሎችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የምንኵስናን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አክብረው ፡ የሚገኙት ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፤ ከዋናው ፡ ከመ ምሪያው ፡ መንበር ፡ ዝ ምሮ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ በመንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ተልእኮ ፡ ላይ ፡ እስከሚገኙት ፡ የማኅበሩ ፡ ዘርፍ ፡ (ቅርንጫፍ) ፡ ልኡካን ፡ ድረስ ፡ መነኮሳት ፡ ከሆኑ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩበት ፡ የተወሰነ ፡ ገለልተኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ የሌለው ፡ አይገኝም ።

፫ ፤ የኛም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለፈው ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ በመልክ ፡ በቋንቋ ፡ በማይመስሏት ፡ በባዕዳን ፡

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

አስተዳደር ፡ ሥር ፡ መኖሯ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆንም ፡ ዛሬ ፡ ባዲሱ ፡ ዘመን ፡ በደገኛው ፡ መሪዋ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ባገኘችው ፡ መብት ፡ የመሪነትን ፡ ዕድል ፡ ካገኘች ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ሰቧን ፡ አስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ማሻሻል ፡ እንደሚኖርባት ፡ በዘመናዊው ፡ ፍጥረት ፡ ቃል ፡ በየውይይቱ ፡ ሲነገር ፡ የሚሰማ ፡ ነው ።

፱ ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍም ፡ ምንት ፡ ብከ ፡ ዘኢነሣእከ ፡ እምካልእከ ፡ ይላልና ፡ ሥርዐቱን ፡ በተግባር ፡ አውለውት ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሲጠቀሙበት ፡ ከኖሩት ፡ ወገኖች ፡ የአመራር ፡ አብነት ፡ መውሰድም ፡ ታላቅ ፡ የማስተዋልና ፡ የጥበብ ፡ ተግባር ፡ ነው ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ መናቅ ፡ ከመሻሻል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያስቀራል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ያባት ፡ ምክር ።

፩ ፤ የተወደዳችሁ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፤ አበው ፡ መነኮሳት ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ተለይተው ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ መኖርን ፡ የመረጡት ፡ ጋብቻን ፡ በመንቀፍ ፡ ሳይሆን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቸርነቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ የፍጹምነትን ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ ባላቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ዐላማ ፡ መሆኑን ፡ ከመጀመሪያው ፡ ዠምረን ፡ በየምዕራፉ ፡ አስረድተናል ፤ ይህም ፡ የመንፈሳዊ ፡ ተዐቅቦ ፡ አስተዳደር ፡ በገዳም ፡ ከሚኖሩ ፡ መነኮሳት ፡ ይዞ ፡ ለሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ አገልግሎት ፡ እስከ ፡ ተሰማሩት ፡ የሃይማኖት ፡ መሪዎች ፡ ድረስ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ እንደሚገባ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ምክሩን ፡ አበርክተናል ።



፪ ፤ ይኸውም ፡ የምንኵስና ፡ ገድል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ከፈቀድኽ ፡ ያለኽን ፡ ሁሉ ፡ ሸጠኽ ፡ ለድኾች ፡ ስጥ ፤ በሰማይ ፡ መዝገብ ፡ ታገኛለኽ ፤ መጥተኽም ፡ ተከተለኝ ፡ ያለውን ፡ ቃል መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡ (ማቴ ፲፱ ፡ ፳፩) ። ይህን ፡ የፍጹምነት ፡ ትምህርት ፡ ከሥጋዊ ፡ ምኞት ፡ ሁሉ ፡ ተለይተው ፡ የሚያገለግሉት ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሰማያዊ ፡ ጸጋና ፡ ክብር ፡ ለመቀበል ፡ ባላቸው ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚታመን ፡ ነው ።

፫ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ይህን ፡ የጌታችንን ፡ ቃል ፡ አብነት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ደናግል ፡ አብራርቶ ፡ ባስተማረበት ፡ አንቀጽ ፡ እኔስ ፡ ያለሐዘን ፡ ልትኖሩ ፡ እወድላችኋለሁ ፤ ሚስት ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ በሚያሰኘው ፡ ገንዘብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግለዋል ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፴፪) ። ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ምክር ፡ በመከተል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሥጋዊ ፡ ኑሮ ፡ በልጅና ፡ በሚስት ፡ ፍቅር ፡ ከመደሰትና ፡ በሀብት ፡ በከብት ፡ ከብሮ ፡ ከመኖር ፡ ይልቅ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከምናገኘው ፡ የሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ፡ ተለይተን ፡ በሰውነታችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያገለገልን ፡ ብንኖር ፡ ጌታችን ፡ በሰጠው ፡ ተስፋ ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት የሚገኘው ፡ ለዘላለም ፡ የማያልፍ ፡ ዋጋ ፡ ይበልጥብናል ፡ ብለው ፡ ብፁዓን ፡ መነኮሳት ፡ በፈቃዳቸው ፡ የሚሸከሙት ፡ ኀይለኛ ፡ ገድል ፡ ነው ።

፬ ፤ በዚህም ፡ በምንኵስና ፡ ተጋድሎ ፡ ትሩፋት ፡ ብዙ ፡ አበው ፡ ተጠቅመውበታል ፤ ብዙ ፡ ተአምራት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለማድረግ ፡ የደረሱም ፡ አሉ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ አባቶችም ፡ በጸሎት ፡ ዐጽፋቸውን ፡ ዘርግተው ፡ (ጀልባ ፡ አድርገው) ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ የተሻገሩ ፡ አሉ ፤ የሐይቅን ፡ ባሕር ፡ በእሳት ፡ ያቃጠሉ ፡ ድውይ ፡ የፈወሱ ፡ ሙት ፡ ያስነሡ ፡ አበው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ገድላቸው ፡ ይነግረናል ፤ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በዘመናችን ፡ ዓለምን ፡ መንነው ፡ በበኣት ፡ ተዘግተው ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በቊመት ፡ በስግደት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየለመኑ ፡ የሚኖሩ ፡ አበው ፡ በየገዳማቱ ፡ እንደሚኖሩ ፡ የሚታመን ፡ ነው ።

፳ ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ በዚህ ፡ በምንኵስና ፡ ሕግ ፡ ተመርተው ፡ ከዓለማዊው ፡ ፍትወት ፡ ሁሉ ፡ ተለይተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሥጋቸው ፡ እያገለገሉ ፡ ሊኖሩ ፡ ነፍሴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥጋዬን ፡ ለማኅበር ፡ ሰጥቻለሁ ፡ በማለት ፡ ቃል ፡ ገብተው ፡ እኩሉ ፡ በተባሕትዎ ፡ (ብቸኝነት) ፤ እኩሉ ፡ በጸሎት ፡ በቅዳሴ ፤ እኩሉም ፡ በሽተኛን ፡ በማስታመም ፡ ደካማውን ፡ በመርዳት ፡ ሁሉም ፡ በየዕድላቸው ፡ ለምንኵስና ፡ ገድል ፡ ተፀምደው ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ደጋግ ፡ አባቶች ፡ እንዳሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ስለ ፡ አመንኳሽ ፡ መብት ።

፩ ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የፈቃድ ፡ ገድለኞች ፡ መነኮሳትን ፡ ተግባር ፡ ገልጸናል ፤ ከዚህ ፡ ቀጥለንም ፡ ስለ ፡ ምንኵስና ፡ አሰጣጥ ፡ ደንብ ፡ እናሳያለን ፤



የምንኵስና ፡ ሕግ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ እንደ ፡ መሆኑና ፡ ሰጭው ም ፡ የገዳሙ ፡ መሥራች ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በየምዕራፉ ፡ የተነገረ ፡ ነው ።

፪ ፤ በኢትዮጵያችንም ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እያደረ ፡ በልማድ ፡ ተሸፍነው ፡ የሚኖሩ ፡ ነገሮች ፡ ይታያሉ ፤ እነሱም ፡ የመነኮሳት ፡ ብዛትና ፡ የመነኮሱበትም ፡ ገዳም ፡ ያለመታወቁ ፡ ናቸው ።

ቆብ ፡ መስጠት ፡ የሚገባው ፡ ለገዳማት ፡ አበ ፡ ምኔቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ቅስናና ፡ ድቁና ፡ የመስጠት ፡ የሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ መብት ፡ ለጳጳሳት ፡ የተጠበቀ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ የምንኵስና ፡ መዓርግ ፡ የሆኑትን ፡ ቆብና ፡ ቅናት ፡ ዮሐንስ ፡ የመስጠት ፡ መብትም ፡ ለገዳም ፡ አበ ፡ ምኔቶች ፡ የተጠበቀ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ፤ (በምንኵስናው ፡ ሕግ ፡ ማለቴ ፡ ነው) ።

፫ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ባዲስ ፡ አበባና ፡ በየገጠሩም ፡ የሚታየው ፡ አመንኳሹና ፡ የመነኮሱበት ፡ ገዳም ፡ ባልታወቀ ፡ ሁናቴ ፡ የመነኵሴና ፡ የመነኵሲት ፡ ብዛት ፡ ከወዴት ፡ መጣ ?

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በየዝክሩና ፡ በየተዝካሩ ፡ ደጃፍ ፡ ሰፍሮ ፡ የሚታየው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መልካም ፡ ዝናና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ያመንኳሽንም ፡ ታሪክ ፡ የሚያስጠላው ፡ የመነኵሴና ፡ የመነኵሲት ፡ ብዛት ፡ አመንኳሹ ፡ ማነው ፤ ገዳሙስ ፡ ወዴት ፡ ነው ?

፬ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ልማድ ፡ ያፈራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የአበው ፡ ሕግ ፡ አልነበረም ፤ ሕገ ፡ አበው ፡ አይደግፈው

www.ethiopianorthodox.org

ምና ፡ ይህን ፡ የልማድ ፡ አረም ፡ በሕገ ፡ አበው ፡ ማረም ፡ ያሻል ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ማረም ፡ ከአበው ፡ የቈየ ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ ነውና ፤ ማሻሻሉ ፡ ባልከፋም ።

፭ ፤ የአበው ፡ መነኮሳት ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ አጽንዖ ፡ በኣት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ አበው ፡ ሥርዐት ፡ ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ መነኰሴ ፡ ከገዳሙ ፡ ወጥቶ ፡ በዓለማውያን ፡ ውስጥ ፡ እንዳይኖር ፡ ክልክል ፡ ነው ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ መነኰሴ ፡ ከደብሩ ፡ ዓሣ ፡ ከባሕሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሕይወት ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ፡ ይላሉና ፤ የአበው ፡ ውሳኔ ፡ ከጥንቱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሆን ፤ ይልቁን ፡ ዛሬ ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅንአት ፡ የኀሊናው ፡ ስሜት ፡ በደከመበት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በተናቀበት ፡ በስምንተኛው ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሌለበት ፡ ኑሮ ፡ መኖር ፡ ጊዜው ፡ ስለማይፈቅድ ፡ እውነትን ፡ ከመናገር ፡ ተገቢውን ፡ ተግባር ፡ ከማሻሻል ፡ ችላ ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ አይኖርም ፤ አበው ፡ ያቈዩትን ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅርስ ፡ አክብሮ ፡ መጠበቅ ፡ ኀላፊነትን ፡ ይጠይቃል ፤ ሕግ ፡ ካልተሠራበት ፡ ሕጋዊ ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውም ።

፮ ፤ ስለዚህ ፡ እንደሚታየው ፡ የዓለማዊና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ሰፈር ፡ ባልተወሰነ ፡ ሁናቴ ፡ ልዩነት ፡ በሌለው ፡ ኑሮ ፡ በዓለም ፡ ባሕር ፡ ተነክሮ ፡ የልብስን ፡ መለዮ ፡ ብቻ ፡ ተጐናጽፎ ፡ በዓለማውያን ፡ መካከል ፡ ተደባልቆ ፡ መኖር ፡ ሕገ ፡ አበውን ፡ መደለል ፡ ይሆናል ፤ በዘመናዊው ፡ ትውልድ ፡ ዘንድም ፡ የልብን ፡ ትዝብት ፡ ከመፍጠሩም ፡ ሌላ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መልካም ፡ ታሪክ ፡ የሚያበላሽ ፡



ነውና ፡ ሁሉን ፡ በየመልኩ ፡ መምራት ፡ የመሪነት ፡ ጕዳይ ፡ በመሆኑ ፡ ቢታሰብበት ፡ ደግ ፡ ነው ።

፯ ፤ ይህንም ፡ ስንል ፡ አበው ፡ ያቈዩት ፡ የምንኵስና ፡ ቅርስ ፡ ይቅር ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ አይኖርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ያስተዳደርን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መጠንቀቅ ፡ ግዴታ ፡ ሕግ ፡ ነውና ፤ ነፍሴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥጋዬን ፡ ለማኅበር ፡ ሰጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ምንኵስናን ፡ የመረጠ ፡ መነኰሴ ፡ ከሆነ ፡ አኗኗሩም ፡ በአበው ፡ ሕግ ፡ የጸና ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ እንላለን ።

፰ ፤ እንኳንስ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰውና ፡ ግዕዛን ፡ ለሌላቸው ፡ ለእንስሳት ፡ ስንኳ ፡ በየመንጋው ፡ የመኖር ፡ ሕግ ፡ አለ ፤ የቀንድ ፡ ከብትን ፡ ከጋማ ፡ ከብት ፡ ፍየልን ፡ ከበግ ፡ ለይቶ ፡ ሁሉንም ፡ በየመልኩ ፡ የተለየ ፡ መኖሪያ ፡ በረት ፡ ወይም ፡ ጕረኖ ፡ አበጅቶ ፡ ማኖር ፡ እንደሚያሻ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ይልቁንም ፡ ከሥጋዊ ፡ ዓለም ፡ በብፅዐት ፡ የተለዩ ፡ መንፈሳውያን ፡ አባቶች ፡ እንደ ፡ አበው ፡ ውሳኔ ፡ በገዳማቸው ፡ ውስጥ ፡ ተወስነው ፡ ሊኖሩ ፡ እንዴት ፡ አይገባቸውም ።

፱ ፤ ይህ ፡ ሁናቴ ፡ እጅግ ፡ አሳሳቢ ፡ ነውና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመንፈሳውያን ፡ አባሎቿን ፡ አኗኗር ፡ በማሻሻል ፡ መንፈሳውያን ፡ ቤተ ፡ ሰቧ ፡ ከሥጋውያን ፡ የሚለዩበትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በማደራጀት ፡ ለዘመኑ ፡ የሚመጣጠን ፡ አስተዳደር ፡ አዘጋጅታ ፡ ቤተ ፡ ሰቧን ፡ በሕግ ፡ መምራት ፡ ይገባታል ፡ ብለን ፡ እናሳስባለን ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

# ጥልቅ ፡ ማስጠንቀቂያ ።

፩ ፡ የውሳጣዊ ፡ ኅሊና ፡ ስሜትና ፡ የሰብአዊ ፡ ሕግ ፡ ፍርድ ፤ በሰው ፡ ልማድና ፡ በይሉኝታ ፡ ባህል ፡ ካልተመራን ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የተመለከትን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቃላችሁ ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ ማለት ፡ ይሁን ፤ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ግን ፡ የክፉ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ የጌታችንን ፡ ትእዛዝ ፡ በተግባር ፡ እናውለው ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ይሆንብናል ።

፪ ፤ ሰዎች ፡ ሆይ ፤ እናስተውል ፤ በሰብአዊ ፡ አስተያየትም ፡ እንመልከት ፤ ያው ፡ በገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ጌታችንን ፡ ስንኳ ፡ ለመፈተን ፡ የደፈረው ፡ የሰው ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ (ሰይጣን) ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሰውን ፡ ከደግ ፡ ምግባር ፡ ሁሉ ፡ ለማሳሳት ፡ ከመታገል ፡ የሚያቋርጥበት ፡ ሰዓትና ፡ ዕለት ፡ የለውም ፤ ስለዚህም ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ደኅንነት ፡ የመጣበትን ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ ከዓለም ፡ የሚያርግበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቃረበ ፤ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ አስጠንቅቋል ።

፫ ፤ የጌታችን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ቃል ፤ «ስምዖን ፡ ሆይ ፤ ሰይጣን ፡ እንደ ፡ ስንዴ ፡ ያበጥራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ተመኘ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እምነትኽ ፡ እንዳይጐድል ፡ ስላንተ ፡ ለመንሁ ፤ አንተም ፡ ተመልሰኽ ፡ ወንድሞችኽን ፡ አጽናና ፡ ብሎታል ፡ (ሉቃ ፳፪ ፡ ፴፩-፴፪) ።



ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ከጌታው ፡ በታዘዘው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይመክራል ፤ «እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ዐዋቆች ፡ ሁኑ ፤ ልቡናችሁንም ፡ በዕውቀት ፡ አጽኑ ፤ ጠላታችሁ ፡ ሰይጣን ፡ የሚውጠውን ፡ ሽቶ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይጮኻልና ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቋል » ፡ ፩ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፰) ። ይህም ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከጸላኤ ፡ ሠናያት ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ በትግልና ፡ በታላቅ ፡ ፈተና ፡ ላይ ፡ እንደሚኖር ፡ የሚያስረዳን ፡ ነውና ፤ የሰይጣን ፡ ድቀት ፡ ባገኘው ፡ በተሳሳተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዳንፈርድ ፡ ያስጠነቅቀናል ፤ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የዚህ ፡ የክፉ ፡ ባለጋራ ፡ ሰይጣን ፡ ፈተና ፡ የማይዋጋው ፡ አይገኝም ። ከሞት ፡ በቀር ፡ የሚለየን ፡ የለም ፤ በዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ አንለያይም ፤ አብረን ፡ እንኖራለን ፡ ብለው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ የተሳሰሩትን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ስንኳ ፡ ባላጡት ፡ ነገር ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ አስፈርሶ ፡ የሚያለያያቸው ፡ (የሚያፋታቸው) ፡ ይኸው ፡ የሰይጣን ፡ አሳችነት ፡ ነው ።

፬ ፤ እንደዚሁም ፡ ከዓለማዊ ፡ ተግባር ፡ ርቄ ፡ ንጽሕናን ፡ ጠብቄ ፡ በመኖር ፡ የመላእክትን ፡ ኑሮ ፡ እኖራለሁ ፤ ሰውነቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ ሰጥቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ገዳም ፡ ገብቶ ፡ ነፍሴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥጋዬን ፡ ለማኅበር ፡ ሰጥቻለሁ ፤ ከዕለት ፡ ጉርሥና ፡ ካመት ፡ ልብስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የግል ፡ ጥሪት ፡ አላበጅም ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ የገባውን ፡ መነኵሴም ፡ ከገዳሙ ፡ አስወጥቶ ፡ የገባውን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቃል ፡ አስፈርሶ ፡ በሥጋዊ ፡ ፍትወት ፡ ሲልከሰከስ ፡ የሚያስገኘውም ፡ ይኸው ፡ የሰው ፡ ጠላት ፡ የሰይጣን ፡ ፈተና ፡ አሸንፎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዲያፈርስ ፡ በሰው ፡ ዘንድም ፡ ኀፍረትና ፡ ውርደት ፡ እንዲለብስ ፡ ወዶ ፡ አይደለም ።

፫ ፤ ከዚህም ፡ ከሰይጣን ፡ ፈተና ፡ የተነሣ ፤ ፍትወታት ፡ እኩያት ፡ የተቃወሟቸው ፡ ከቀደሙት ፡ አበውም ፡ አካላቸውን ፡ ቈርጠው ፡ ዐይናቸውን ፡ አፍርጠው ፡ እስከ ፡ መጣል ፡ ደርሰው ፡ የሰይጣንን ፡ ፈተና ፡ አሸንፈው ፡ ድልን ፡ እንዳገኙ ፡ ዜና ፡ አበው ፡ ያስረዳል ። የመሸነፍ ፡ ዕድል ፡ እየገጠማቸው ፡ ካልሆነ ፡ አኳኋን ፡ የደረሱ ፡ እንደ ፡ ነበሩም ፡ የአበው ፡ ታሪክ ፡ ያስረዳል ።

፬ ፤ ከዓለማዊም ፡ ኑሮ ፡ ምሳሌን ፡ ብንወስድም ፡ በወታደራዊ ፡ ሕግ ፡ አገሩን ፡ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ ለመጠበቅ ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ የዘመተ ፡ ወታደርም ፡ ሁሉ ፡ ድልን ፡ አያገኝም ፤ ብዙዎቹ ፡ በጀግንነት ፡ ተዋግተው ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ተቀዳጅተው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ሲገቡ ፡ ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ኀፍረት ፡ ለብሰው ፡ የሚመለሱና ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ተማርከው ፡ የሚቀሩም ፡ እንዳሉ ፡ የሚታወስ ፡ ነው ። በጨዋታ ፡ ሜዳ ፡ ስንኳ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሸንፍ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲሸነፍ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ፤ የመንፈሳዊው ፡ ትግልም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። የሰው ፡ ፍጥረት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እየወደቀም ፡ እየተነሣም ፡ የትግል ፡ ኑሮ ፡ እንደሚኖር ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፤ በተሸነፈ ፡ መነኰሴ ፡ ሊፈረድበት ፡ አይገባም ።



ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

## ስለዚህ ፡ አበው ፡ እንደሚከተለው ፡ ውሳኔ ፡ ወስነዋል ።

(ሀ) መነኰሴ ፡ ድቀት ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ንስሓ ፡ ተቀብሎ ፡ በመዓርጉ ፡ ተመልሶ ፡ በምንኵስናው ፡ እንዲጸና ፡ አዘዋል ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናውን ፡ ነቅፎ ፡ (ንቆ) ፡ በዓለም ፡ ሊኖር ፡ ወዶ ፡ ከምንኵስና ፡ ሥርዐት ፡ የወጣ ፡ ከሆነ ፡ ሕዝባውያኑን ፡ መስሎ ፡ ይኑር ፡ እንጂ ፤ ሕዝባውያኑን ፡ መስሎ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ በመነኮሳት ፡ አርአያ ፡ ሊኖር ፡ አይገባውም ፡ የሚል ፡ ውሳኔ ፡ አለ ። «ወለእመ ፡ ወፅአ ፡ እኁ ፡ እምኔት ፡ መኒኖ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናሁ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡ ወብሔር ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ህየ ፡ ይኩን ፡ በመዓርገ ፡ ሕዝባውያን ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፤ ወኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትመሰል ፡ በመነኮሳት ፡ ዘእንበለ ፡ በአምሳለ ፡ ሕዝባውያን» ፡ (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ ገጽ ፡ ፹፯) ። በውሳጣዊ ፡ መንፈሱ ፡ በዓለማዊ ፡ ፈቃድ ፡ ተሸንፎ ፡ ፍጹም ፡ ውድቀት ፡ የወደቀና ፡ በንስሓ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ለመመለስ ፡ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ መልአክ ፡ ነበርኩ ፡ ሰው ፡ ሆንኩ ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ ውድቀቱን ፡ ገልጾ ፡ ተመልሶ ፡ በዓለማዊ ፡ ግብር ፡ መኖሩን ፡ ከመረጠ ፡ የሰብአዊ ፡ ባሕርዩን ፡ መብት ፡ ሳይነፈግ ፡ (ሳይከለከል) ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዐት ፡ ሕዝባውያን ፡ በሚኖሩበት ፡ ሕግ ፡ እንዲኖር ፡ የአበው ፡ ብያኔ ፡ ያሰናብታል ።

(ለ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ስለ ፡ ድንግልናው ፡ ያፈረ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የወደደውን ፡ ያድርግ ፡ ቢያገባም ፡ ኀጢ

www.ethiopianorthodox.org

ጋብቻን ፡ ቅድስና ፡ ስለሚነግረን ፤ ይቻለኛል ፡ ብሎ ፡ በድንግልና ፡ መኖርን ፡ የመረጠ ፡ ሰው ፡ በንጽሕና ፡ መኖሩ ፡ ሳይቻለው ፡ ቀርቶ ፡ ብፅዐቱ ፡ በተሰናከለበት ፡ ጊዜም ፡ ደካማነቱን ፡ አምኖ ፡ በሥጋዬ ፡ አገለግልኻለሁ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያደረገውን ፡ ብፅዐቱን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ኀጢአቱን ፡ ተናዞ ፡ አበው ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ በምንኵስና ፡ መኖር ፡ ሳይቻለው ፡ ቀርቶ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ዓለማዊ ፡ ፈቃድ ፡ የገባ ፡ መነኵሴ ፡ ሕዝባውያኑን ፡ መስሎ ፡ ይኑር ፡ ባሉት ፡ ብያኔ ፡ በክርስቲያናዊ ፡ ሥርዐት ፡ የተፈጥሮ ፡ ዘመዶቹን ፡ መስሎ ፡ መኖር ፡ እንደማያሳፍር ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በሠለስቱ ፡ ምእቱ ፡ ብያኔ ፡ ታውቋል ።

፪ ፤ ስለዚህ ፡ በማያሳፍረው ፡ ተግባር ፡ አፍሮ ፡ ይልቁን ፡ ባሳፋሪ ፡ ሁናቴ ፡ መኖር ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ራስን ፡ መበደል ፡ ስለሚሆን ፡ ከሁለቱም ፡ ሕግ ፡ አንዱን ፡ ሳይዙ ፡ ከእውነት ፡ ሸሽቶ ፡ መኖር ፡ የባሰ ፡ ኀጢአት ፡ መሆኑን ፡ በዐይነ ፡ ልቡና ፡ ማስተዋል ፡ እንደሚያሻ ፡ እናሳስባለን ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠን ፡ መንፈስ ፡ በዐይነ ፡ ልቡና ፡ ስንመለከተው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰው ፡ ችሎታ ፡ በላይ ፡ አይደለም ፤ ፈጣሪ ፡ አምላክ ፡ ሰውን ፡ ጽኑ ፡ ሸክም ፡ አላሸከመውም ፤ እንዲያውም ፡ የደግነቱ ፡ ብዛት ፡ «እናንተ ፡ ደካሞች ፡ ሸክማችሁ ፡ የከበደ ፡ ሁሉ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፤ እኔም ፡ አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን ፡ (ሕጌን)፡ በላያችሁ ፡ ተሸከሙ ፤ ከኔም ፡ ተማሩ ፤ እኔ ፡ የዋህ ፡ በልቤም ፡ ትሑት ፡ ነኝና ፤ ለነፍሳችሁም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛላችሁ ፤ ቀንበሬ ፡ ልዝብ ፡ ሸክሚም ፡ ቀላል ፡ ነውና ፡ እያለ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይጠራል ። ይህን ፡ የአምክ ፡ ጥሬ ፡ አልሰማ ፡ አላስተውል ፡ ብሎ ፡ መቸገር ፡ የሚያሳ



ዝን ፡ ነው ፤ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ትእዛዛት ፡ የሚመራ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ሊያገኘው ፡ አይችልም ፤ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይቅርታና ፡ ምሕረት ፡ ነውና ።

፫ ፤ በሰው ፡ ልማድ ፡ ስንመለከተውም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለትሩፋት ፡ ብሎ ፡ ያነሣው ፡ ሸክም ፡ አልቻል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ሸክሙን ፡ ከራሱ ፡ አውርዶ ፡ ቢያሳርፈው ፡ ያለችሎታው ፡ አልተሸከመም ፡ ብሎ ፡ የሚፈርድበት ፡ አይገኝም ፤ የባሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሰነፍ ፡ ዱሮውንስ ፡ ያላቅሙ ፡ ማን ፡ ተሸከም ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ ያፌዝበታል ፡ እንጂ ፤ ሸክሙ ፡ እንደ ፡ ተጫነው ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ የሚፈርድበት ፡ ፍጡር ፡ አይኖርም ።

፬ ፤ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የፍጹምነትን ፡ ክብር ፡ አገኝ ፡ ብሎ ፡ የተሸከመውን ፡ ባሕርያዊ ፡ ፈቃድ ፡ አልቻለው ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ሸክሙ ፡ እንደ ፡ ከበደኽ ፡ ኑር ፡ አላለም ፤ ይኸውና ፡ ሸክም ፡ የከበዳችሁ ፡ ሁሉ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ እኔም ፡ አሳርፋችኋለሁ ፡ እያለ ፡ ደካሞችን ፡ ለዕረፍት ፡ ይጠራናል ፤ ቸር ፡ ነውና ።

በጌታችን ፡ ቃል ፡ የተነገሩ ፡ ዐበይት ፡ ኀጣውእ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

አትግደል ፤

አታመንዝር ፤

አትስረቅ ፤

በሐሰት ፡ አትመስክር ፤

አባትና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤

ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ።

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህንና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ የሰው ፡ ፍጥረት ፡
በተላላፊነቱ ፡ የሚሠራቸውን ፡ ኀጣውእ ፡ እንኳ ፡ ሠርቶ ፡
ቢገኝ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቅርታና ፡ ምሕረትን ፡ በመለ
መን ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ተጸጽቶ ፡ በንስሓ ፡ ቢመለስ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ እንደሚለው ፡ ይኸውና ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚለንን ፡ እንስማው ። «መሰናከል ፡
ግድ ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መሰናክሉን ፡
ለሚያመጣው ፡ ወዮለት ፤ (አሰናካዩ ፡ ሰይጣን ፡ ነው) ፤
ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ ከሚያሰናክል ፡ ይልቅ ፡
የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ ባንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ቢጣል ፡
ይሻለው ፡ ነበር ፤ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

# የአምላክ ፡ ይቅርታና ፡ ስርየት ።

ወንድምኽ ፡ ቢበድልኽ ፡ ገሥጸው ፤ ቢጸጸትም ፡
ይቅር ፡ በለው ፤ በቀንም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ቢበ
ድልኽ ፡ በቀንም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ተጸጸትሁ ፡ እያለ ፡
ወደ ፡ አንተ ፡ ቢመለስ ፡ ይቅር ፡ በለው ፡ (ሉቃ ፲፯ ፡ ፬) ፡
እያለ ፡ ይቅር ፡ ባይና ፡ ርኅሩኅነቱን ፡ ይገልጽልናል ።
ስለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአትስ ፡ የሚሆን ፡ በሠራው ፡ ኀጢ
አት ፡ በንስሓ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቅርታን ፡ አለመሻት ፡
ነው ፡ እንጂ ፤ ማናቸውንም ፡ የኀጢአት ፡ ዐይነት ፡ ቢሠ
ራም ፡ በደለኛው ፡ ሰው ፡ በንስሓ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከቀረበ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ የማይሰረይ ፡ ኀጢ
አት ፡ እንደማይኖር ፡ ጌታችን ፡ በቃሉ ፡ ይነግረናል ።



«በኀጢአታችን ፡ ብንናዘዝ ፡ ኀጢአታችንን ፡ ይቅር ፡
ሊለን ፡ ከዐመፅም ፡ ሁሉ ፡ ሊያድነን ፡ የታመነና ፡ ጻድቅ ፡
ነው» ፡ (፩ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፱ )።

ምንዝርስና ፡ ግን ፡ ጥንቱም ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ የፍጹ
ምነትን ፡ ክብር ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ በሰውነት ፡ የሚደ
ረግ ፡ ብፅዐት ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ እፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ የገ
ባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በማፍረሱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ቢሆንም ፡
ቢቻለው ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ንስሓ ፡ ተቀብሎ ፤ የገ
መረውን ፡ ገድሉን ፡ ቢፈጽም ፡ የበለጠ ፡ ይሆናል ፤ ጨርሶ
በመንፈሱ ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ የቀደሙት ፡
አበው ፡ ምንዝርስና ፡ የፈቃድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የግዴታ ፡
አይደለም ፡ እንዳሉት ፡ ነውና ፡ የብርሃኑን ፡ በጨለማ ፡
ከመሻት ፡ ይልቅ ፡ ንስሓ ፡ ገብቶ ፡ በአዳም ፡ ሕግ ፡ ኑሮ ፡ ቢ
ኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቅርታና ፡ ምሕረት ፡ እንደማይነ
ፈገው ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያስተምራሉ ። «በድንግል
ናው ፡ የፈራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የወደደውን ፡ ያድርግ ፡
ቢያገባም ፡ ኀጢአት ፡ የለበትም» ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰) ።

ተጽሕፈ ፡ በመዋዕለ ፡ ስደት ፡ አ ፡ ፊ ፡

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ ።


ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ሕገ ፡ ፈቃድ ፡ ምንኵስና ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ፯

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

መንኖ ፡ ጥሪት ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ፱

ምዕራፍ ፡ ፫ ። ፲፪

ምዕራፍ ፡ ፬ ። ፲፯

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ሥርዐተ ፡ ምንኵስና ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ...... ፲፰

ምዕራፍ ፡ ፮ ። ፳፩

ምዕራፍ ፡ ፯ ። ፳፭

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

ያባት ፡ ምክር ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ፳፮




ማውጫ ።


ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

ስለ ፡ አመንኲሽ ፡ መብት ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ፳፰

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ጥልቅ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ፴፪

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ውሳኔ ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ፴፭

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

ብያኔ ፡ ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ...... ፴፮

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

የአምላክ ፡ ይቅርታና ፡ ስርየት ፡ ...... ...... ...... ...... ፵


www.ethiopianorthodox.org